ለካርሎስ ሮዛርዮ ት/ቤት ምዝገባ የሚያስፈልጉ ሰነዶች ዝርዝር ጠቋሚ መረጃ

ካርሎስ ሮዛርዮ ት/ቤት ለመመዝገብ የሚያስፈልገውን የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫ ሰነድ ለማቅረብ ሁለት አማራጮች አሉ። እነዚህ የሰነድ ማረጋገጫ መመሪያዎች የሚወሰኑት እና ተቀባይነታቸው የሚጸድቀው በ ዲሲ ትምህርት ቢሮ(OSSE) ነው። ተቀባይነት ባላቸው ሰነዶች ላይ ለሚነሱ ማናቸውም ጥያቄዎች፣ እባክዎን registration@carlosrosario.org ይጠይቁ ወይም በ 202-797-4700 ይደውሉ።

ሰነዶቹ አንድ አይነት ስም እና አድራሻ ሊኖራቸው ይገባል።

<u>አማራጭ 1 ፦ ከሚከተሉት ውስጥ አንድ ዋና ቅጂ ሰነድ ያቅርቡ</u>

ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ አንድ ሰነድ ብቻ በመምረጥ ከሰነዱ በስተቀኝ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ካሟላ ቅጂውን ማቅረብ ይችላሉ።

<table>
<tr><th>የሰነዱ አይነት</th><th>ሰነዱ ማሟላት ያለባቸው ነገሮች

እባክዎን ሰነዱ የተዘረዘሩትን ሁሉንም መስፈርቶች ማሟላቱን ያረጋግጡ</th></tr>
<tr><td>ሀ. የደሞዝ ወረቀት

ABC VE Firm
Payroll Account
Check #: 123
Date: May. 24, 2020
Pay to the order of Enrolling Person $1,403.56
One-thousand, four-hundred, three dollars and 56/100 Dollars
US Network Bank
Memo: PPE May 24, 2020
Cash Isking
Chief Financial Officer
Sample
Detach check above before depositing and save checkstub below for your records.
ABC VE FIRM
Check #: 123
Date: May 24, 2020
Employee: Enrolling Person
Pay Period: May 13 - 24, 2020
Current YTD
Gross Earnings $1,680.00 $18,480.00
Deductions:
Federal Income Tax $141.38 $503.88
Social Security (FICA) 70.56 200.56
Medicare 24.36 78.36
State (DC) Income Tax 23.34 98.34
State Disability Insurance (SDI) 16.80 $276.44 84.80 $3,040.84
Net Pay $1,403.56 $15,439.16</td>
<td>የዲሲ ግብር እየከፈሉ መሆንዎን ማሳየት አለበት፤ በተጨማሪም የሌሎች ግዛቶች (ሜሪላንድ እና ቨርጂኒያ) ክተካተቱበት ሰነዱ ተቀባይነት አይኖረውም
የከፈሉት ግብር ተቀናሽ መጠን በደሞዝ ወረቀቱ ላይ በግልጽ መጠቀስ አለበት።
የደሞዝ ክፍያ ሰነዱ ባለፉት 45 ቀናት ውስጥ የተከፈለ መሆን ይኖርበታል፤ ከዛ በላይ ከሆነ ተቀባይነት አይኖረውም።</td></tr>
<tr><td>ለ. ጊዜው ያላለፈበት ከዲሲ መንግስት እርዳታ እየተቀበሉ መሆንዎን የሚያሳይ ማረጋገጫ ደብዳቤ

ለምሳሌ : TANF, Medicaid, DC Alliance, Supplemental Security Income

DC Financial Assistance Program
Government of the District of Columbia
1050 First Street NE
Washington, DC 20002
Date: April 1 2020
Account ID: 999999999
Suzy Creamcheese
54 District Street NW
Washington, DC 55555
Subject: ELIGIBILITY FOR DISTRICT OF COLUMBIA FINANCIAL ASSISTANCE PROGRAM
Dear Suzy Creamcheese:
Based on the information you submitted the following individuals are eligible for the financial assistance program:
List of eligible participants:
Relationship — Name
Mother — Suzy Creamcheese
Child — Frank Creamcheese
Child — Lolly Creamcheese
Sample
Your program participation card is free and can be picked up at the following locations:
• Address 1, Washington, DC 20000
• Address 2, Washington, DC 20000
Program eligibility is valid for one year and will expire on 4/1/2021. If you have any questions, please contact us at (555) 555-5555.
ELIGIBILITY WORKER</td>
<td>ሰነዱ ከዲሲ መንግስት እርዳታ እንደሚያገኙ ማረጋገጥ አለበት።
ደብዳቤው ጊዜው ያላለፈበት እና ወቅታዊ መሆን አለበት።
የኢንሹራንስ ካርድ ተቀባይነት የለውም ፤ የነፃ ኢንሹራንስ አገልግሎቱ የተፈቀደበትን ማረጋገጫ ደብዳቤ ይዘው መምጣት</td></tr>
</table>

<table>
<tr>
<td></td>
<td>አለብዎት።
የነፃ ኢንሹራን ማረጋገጫ ደብዳቤው ከሌሎት እና የነፃ አገልግሎቱን እየተጠቀሙ ከሆነ የዲሲ ጤና ቢሮ በ202 724 7491 ደውለው የደብዳቤውን ቅጂ መጠየቅ ይችላሉ።</td>
</tr>
<tr>
<td>ሐ. በዲሲ ታክስ ቢሮ የተረጋገጠ የD40 ታክስ ቅጽ ቅጂ

</td>
<td>በዲሲ የታክስ እና ገቢዎች ቢሮ የተረጋገጠ ቅጂ መሆን አለበት። ሰነዱን ለማረጋገጥ የዲሲ ግብር እና ገቢዎች ቢሮ (1101 4th St SW #270) ሄደው ማህተም ማስደረግ አለብዎት።
ሰነዱ የአሁኑ ወይም የቅርብ ጊዜ ዲሲ ታክስ መክፈልዎን ማረጋገጫ ማስረጃ ሊኖረው ይገባል።
የቅርብ ዓመት መሆን አለበት
የዲሲ የገቢ ግብር ፎርሙ 31ኛ ቁጥር ላይ የሰፈረው ተቀናሽ ከ $0 በላይ መሆን አለበት።</td>
</tr>
<tr>
<td>መ. የኤምባሲ ደብዳቤ፤ አመልካቹ በኤምባሲው ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም በዲሲ የኤምባሲው ንብረት በሆነ ቤት ውስጥ እንደሚኖር የሚያረጋግጥ ደብዳቤ

EMBASSY OF COUNTRY
345 DISTRICT STREET, WASHINGTON, DC 20000
4/1/2020
TO WHOM IT MAY CONCERN:
I, Embassy Official, Human Resources Officer at the Country Embassy in Washington, DC, hereby certify that
SUZY CREAMCHEESE
a Country employee, is assigned to the Country mission in Washington, DC, as Third Secretary since January 2019. As such, Suzy Creamcheese, as well as their spouse, Frank Creamcheese, and their children, Bonnie and Chad, are residing at 1234 District Avenue, Washington, DC 20000 and are housed at no cost to them by the Embassy of Country.
Suzy Creamcheese's mission will end in July 2022.
Sample
Embassy Official
Human Resources</td>
<td>የኤምባሲው አርማ ያለበት፤ እንዲሁም ኦፊሴላዊ የኤምባሲ ማህተም ማካተት አለበት።
ተማሪው በኤምባሲው ንብረት በሆነ ቤት ወይም በኤምባሲው ውስጥ እንደሚኖር ደብዳቤው ላይ መጠቀስ አለበት።
ባለፉት 12 ወራት ውስጥ የተፃፈ መሆን አለበት።
ኦፊሴላዊ የኤምባሲው ሰራተኛ ፊርማ ሊኖረው ይገባል።</td>
</tr>
</table>

<u>አማራጭ 2 ፦ ከሚከተሉት ውስጥ ሁለቱን ሰነዶች መርጠው ዋና ቅጂያቸውን ያቅርቡ</u>

እባክዎን በስተግራ ካሉት ውስጥ ሁለት ሰነዶችን በመምረጥ እና በስተ ቀኝ ከተዘረዘሩት መስፈርቶች ጋር በማመሳከር ተቀባይነት ያላቸውን ሰነዶች ያቅርቡ።

Document Type	Document must include (please make sure every box is checked)
ሀ. ጊዜው ያለፈበት የዲሲ የሞተር ተሽከርካሪ ምዝገባ ካርድ 	• ስም እና አድራሻው ከሁለተኛው የሰነድ ምርጫዎ ጋር መመሳሰል አለበት። • ዋናው ቅጂ መሆን አለበት ወይም የዲሲ ዲኤምቪ ዲጂታል ቅጂ (ከሞባይል አፕ) ሊያሳዩ ይችላሉ። • ጊዜያዊ ካርድ ተቀባይነት የሚኖረው ለአጭር ጊዜ ስለሆነ፣ዋና ሰነዱን በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ማሳየት አለብዎት።
ለ. ጊዜው ያላለፈበት የቤት ኪራይ ስምምነት ውል ከቤት ኪራይ ክፍያ ደረሰኝ ጋር 	• ስም እና አድራሻው ከሁለተኛው የሰነድ ምርጫዎ ጋር መመሳሰል አለበት። • የሊዝ ስምምነት ውሉ ባለቤት መሆን አለብዎት • የሊዝ ዋናው ውል ጊዜው ያለፈበት መሆን የለበትም ። ጊዜው ያለፈበት ከሆነ፥ በአንድ ዓመት ውስጥ የተፈረመ ተጨማሪ የማስተካያ ስምምነት ወይም ከአከራዩ በቅርብ ጊዜ የተፃፈ የነዋሪነት ማረጋገጫ ደብዳቤ እያይዘው ማቅረብ አለብዎት። • በደረሰኙ ላይ ያለው የኪራይ ክፍያ መጠን በሊዝ ውሉ ላይ ከተጠቀሰው የክፍያ መጠን ጋር መመሳሰል አለበት። • ደረሰኙ የኪራይ ክፍያ ኦፊሴላዊ ደረሰኝ መሆን አለበት። • የባንክ ክፍያ ዝርዝር ተቀባይነት አለው ፤ ነገር ግን እንደ ቬንሞ ወይም ካሽ አፕ ያሉ የክፍያ መንገዶች፥ እንዲሁም በእጅ የተፃፈ ደብዳቤ እንደ ደረሰኝ አይቆጠሩም።

ሐ. ጊዜው ያላለፈበት የዲሲ መንጃ ፍቃድ ወይም የዲሲ መታወቂያ ካርድ 	● ስም እና አድራሻው ከሁለተኛው የሰነድ ምርጫዎ ጋር መመሳሰል አለበት። ● በDMV የተሰጠ መሆን አለበት ● ጊዜው ያላለፈበት መሆን አለበት ● ጊዜያዊ መታወቂያ/የመንጃ ፍቃድ ተቀባይነት አለው፣ ነገር ግን ተማሪው ኦፊሴላዊ መታወቂያ/ቋሚ መንጃ ፍቃድ ቅጂውን ከበዲኤምቪ እንደደረሰው ለት/ቤቱ ማቅረብ አለበት።

መ. አንድ የፍጆታ ቢል ከክፍያ ደረሰኝ ጋር (የጋዝ፣ የኤሌክትሪክ ፣ ወይም የውሃ ቢል ከክፍያ ጋር ብቻ)፤ የሞባይል ስልክ እና የኢንተርኔት ሂሳቦች ተቀባይነት የላቸውም።
 	
	● ስም እና አድራሻው ከሁለተኛው የሰነድ ምርጫዎ ጋር መመሳሰል አለበት።
	● ቢሉ ባለፉት ሁለት ወራት ውስጥ የተሰጠ እና የክፍያው ደረሰኝ ለሚያቀርቡት ቢል መሆን አለበት።
	    ● የባንክ ክፍያ ዝርዝር እንደ ደረሰኝ መጠቀም ይቻላል።
	    ● ቬንሞ ወይም ካሽ አፕ ያሉ የክፍያ መንገዶች፥ እንዲሁም በእጅ የተፃፈ ደብዳቤ እንደ ደረሰኝ አይቆጠሩም።